# ተደመሩ አትበሉን

ፈጣን ነው ባቡሩ ፣ ፈጣን ነው ባቡሩ
እንዳያመልጣችሁ ፣ ግቡ ተሳፈሩ
አለን ብዙ ቦታ ፣ ግቡ ተደመሩ
የቀን ጅብም ቢሆን ፣ ይደመር ጨምሩ
መደመር ብቻ ነው ፣ ትግላችን መዝሙሩ
መቀነስ አያውቅም ፣ የሂሳብ ቀመሩ ።

ከሆን ስሌቱ ፣ መደመር በጅምላ
የመጣን መቀበል ፣ ሳይበጅ ከለላ
እንደምረው ካልን ፣ ጠላንም ከአተላ
እያግበሰበስን ፣ እሾህ አሜኬላ
መቀነስ የሚባል ፣ ካላበጀን መላ
ድመራው መቀነስ ፣ ይሆናል ሲሰላ
ሁሉንም ማግበስበስ ፣ እያስከፍላል ኋላ ።

ዘር እንዳይበላሽ ፣ እንዳይሆን ሰለባ
ተንገዋሎ ይለይ ፣ ግርዱ ከገለባ
      አይቀላቀሉም ፣ ዘይትና ውሃ
      ባንዳ አይደመርም ፣ ቢገባም ንሰሃ
የወያኔን አውታር ፣ መረቡን በጣጥሶ
ስልጣን የጨበጠን ፣ በጥርሶቹ ነክሶ
የዘረፉት ንብረት ፣ ባግባቡ ተወርሶ
የጫካውን ሽፍታ ፣ ደደቢት መልሶ
ታጋዩን ደምሮ ፣ ባንዳውን ቀንሶ
ያኔ ህዝብ ይሆናል ፣ ዋልታና ምሰሶ ።

የወንበዴ መንጋ ፣ እጅግ የተናቁ
አገር ያሸበሩ ፣ ገዳይ እያነቁ
ከመቀነስ በቀር ፣ መደመር አያውቁ
እንደ ትላንትናው ፣ እንዳሻ መስረቁ
እንደልብ መዝረፍ ፣ ከብሩም ከወርቁ
ስለቀረባቸው ፣ ከስልጣን ሲወድቁ
መቀሌ መሽገው ፣ ዛሬ ቢደበቁ
ሽሽት ነው አውቀናል ፣ ከህዝብ ይታረቁ
በቁም ከሚሞቱ ፣ እየተሳቀቁ ።

በጥላቻ ስብከት ፣ በሃሰት ያለአግባብ
አንዣቦ አያየነው ፣ የሞት ጥላ ድባብ
ጦር እየታወጀ ፣ በጠባቦች ጠባብ
ተቀናሽ እያለ ፣ መደመር ያለሃሳብ
ህግ ያልተከተለ ፣ የዞረበት ሂሳብ
የማይፀና ቁልል ፣ መደመር የንቧይ ካብ
ሊያዛምዱ መድከም ፣ እርግብን ከእባብ ።

ድንበር እየናዱ ፣ ዜጋን ያፋልሱ
ለህዝባችን ውድቀት ፣ ሞት እየደገሱ
አትፀና ይመስል ፣ አገር ያለነሱ
ከፍራቻ ታይቶ ፣ ህዝብ መታገሱ
ይፎክሩብናል ፣ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ
ባንዳና ምንደኛን ፣ በውል ሳትቀንሱ
አያዳግም በትር ፣ ደህና አርገው ሳይቀምሱ
ተደመሩ አትበሉን ፣ ካሰሱም ገሰሱ ።

አገር ሊበትኑ ፣ ዛሬም እያቅራሩ
ጥራት የጎደለው ፣ ማለት ተደመሩ
የሚዋጥ አልሆነም ፣ ይለወጥ መዝሙሩ
መቀነስ ተምረን ፣ ሁሉም ካልታሰሩ
ለባንዳ መደመር ፣ ካልተዘጋ በሩ
እዬዬ ነው ትርፉ ፣ ግምኛ ሲከስሩ ።

ታዛቢው

August 2, 2018